# <u>የሁኔታችን አሳሳብነትና አሳፋርነት</u>

በዶ/ር ኤረንጎ ቀልብሰው

ለጋራ ጥቅም እንዳንሠራ ስንከፋፈል፣ እየጠፋ የሀሳብ አንድነት፤
ዘላቂ ሰላምን ለተጠማ ሕዝብ፣ ተግባራዊ ዲሞክራሲ ናፍቆቱ ለሆነበት።
እርስ በርስ ሰንዋጋ፣ ዕውቀትና ትምህርት የሌለን ይመስል፤
ሚሊንዩም ለማክበር ስንዘጋጅ፣ ማሸነፍ እያቃተን የኑሮን ትግል።
ስህተት ሲደጋገም፣ እያቃተን ከታሪክ መማር፤
ባለም ስንታወቅ በሰዉ ዕልቂት፣ በደሀነት በችግር።
ሞልቶ እያለ ባገር፣ ብዙ ጥሬ ሀብት፤
የማይገኝ ዕንቁ፣ የሰው ኃይል በብዛት።
“የእናት ሆድ ዥንጉርጉር” እንዲሉ፣ አገር ሆና ባለብዙ ባህል፤
አብረን ኑሮን ለማሸነፍ፣ ጨርሶ ሲጠፋ የእርስ በርስ መቻቻል።
ኑሮ ሲሆን ወገን የሚያሸሽ ካገር፣ እንዳይሞት ፈርቶ ለሕይወቱ፤
ሰዉ ሲካን በክፋት፣ ሌላዉን ሲያደርግ እንዳይኖር በቤቱ።
መልካም እየመሰለ ሁሌ ሲደረግ፣ መሆን የሌለበት፤
መጥፎ መስሎ ሳይደረግ ሲቀር፣ መደረግ ያለበት።
የራሱን ሥራ የሚያደንቅ፣ አመራር ሲፈራረቅበት ሕዝቡ፤
ወገን ሲጠቃ እንደጠላት፣ ስብዕናዉ ሲገፈፍ ተይዞ ወገቡ።
ሕዝቡ ሲተራመስ፣ ሲያልቅ በበሽታ፣ ሲቆላ በችግር፤
ከፊሉ ሲሰደድ፣ ሲታሠር ሲሞት፣ ሲመለስ ወዳፈር።
አጥፊ ድርቅና ጎርፍ ተፈራርቀዉ፣ ሲያወድሙ ንብረትና ሕይወት፤
ሀብታም ተንደላቆ እየኖረ፣ ደሀዉ ግን ባገሩ ሲሞት የቁም ሞት።
የሥራ ፈቱ ብዛት ሲታይ፣ የጎዳና አዳሪው ቁጥሩ ሲጨምር፤
ዜጋ ኑሮው ሲሆንበት ስዖል፣ ማግኘት ተስኖት መሠረታዊ ነገር።
በኤች አይ ቪ/ኤድስ ወገን ሲረግፍ፣ በጨጓራ ሕመም በሌላም ወድቆ ሲቀር፤
ግለሰብ ሲታገል፣ ቤተሰብ ሲያዝን ሲጨነቅ፣ አገር ሲጎዳ አስከሬን ሲቀበር ።
መከራ ሲበዛበት ሰዉ፣ ኑሮ ሲሆንበት ትርጉም የለሽ እንቆቅልሽ፤
ለአመራሩ ሲጠፋ መካሪ፣ “እንደዚህ አይደረግ!” ባይ ህሊና ወቃሽ።
ታማሚዉ ብቻ ሳይሆን፣ ለማኝ ሲሆን አገር በሙሉ፤
ምጣኔ ሀብት ሲዳሽቅ፣ አመራሩ ወገን ጠፍቶት ዉሉ።
ችግራችን መፍትሔ እንዳይኖረዉ፣ መቻቻል እያጣን አንድነት፤
በመናናቅ፣ በቂም በቀል፣ ጊዜያችን ሲባክን በታወረ ግለኝነት።
ራስ መምራት የማንችል ይመስል፣ ባገር ሞልቶ ምሁር፣ ባለጠቃሚ ዕውቀት፤
ቆርጠ መነሣት ተስኖን፣ ልመናን ስንመረጥ፣ እንደማልማት ያን ድንቅ መሬት።
እንደ ቢቢሲ ዘገባ፣ ስድስት ሚሊዮን ሕፃናት፣ ለጉዲፈቻ ሲቀርቡ፤
የአገሪቷ ተስፋ በዕምቡጡ ሲቀጭ፣ ችግራችን በዝቶ፣ ሲያልፍ ከገደቡ።
በፓርቲ በብሔር እያልን፣ ለቢሮ ስንሮጥ፣ በኑሮ መከራ ሲንገላታ ወገን፤
የሕዝብ ቢሮ ሲዉል ለግል ጥቅም፣ ደሃ ለመበዝበዝ፣ ሌላ ለመጨቆን።
እንዲያዉ ሁኔታችን ሲታይ፣ “እኔ ሞቼ ሰርዶ አይብቀል!” እየሆነ፤
መከባበር መደማመጥ እየጠፋ፣ ተስፋችን ሳይጨበጥ ባየር በነነ።
ህሊና ላለዉ፣ የኛ ሁኔታ በእዉን ያሳስባል፤
የወገን ችግርና ዕልቂት፣ እጅግ ያሳፍራል።

(**ለአስተያየት:** ekelbisow@yahoo.com)